# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ አምተኛ ዓመት ቁጥር ፸፬
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፬ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

ኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No. 74
ADDIS ABABA July 31 th, 2019


**ማውጫ**


አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፵፱/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

ለሴቶች የንግድ ሥራ ፈጠራ ብቃት ማሳደጊያ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር............ገጽ፲፩ሺ፫፻፸፮


**CONTENT**


Proclamation No.1149/2019

European Investment Bank Loan Agreement for Financing Women Entrepreneurship Development Program Ratification Proclamation...................................Page 11376


**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፵፱/፪ሺ፲፩**

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጸደቅ የወጣ አዋጅ**

ለሴቶች የንግድ ሥራ ፈጠራ ብቃት ማሳደጊያ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ፴ ሚሊዮን ዩሮ (ሠላሳ ሚሊዮን ዩሮ) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ መካከል ህዳር ፲ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም በአዲስ አበባና በሉግዘምበርግ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፮ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**PROCLAMATION NO. 1149/2019**
**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE EUROPEAN INVESTMENT BANK**

**WHEREAS**, the Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the European Investment Bank stipulating that the European Investment Bank provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of 30,000,000 Euro (Thirty Million Euro) for financing Women Entrepreneurship Development Program, was signed in Addis Ababa and Luxembourg on 19th Day of November 2018;

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 13th Day of June 2019;

**NOW, THERFORE**, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

**፩.<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለሴቶች የንግድ ሥራ ፈጠራ ብቃት ማሳደጊያ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፵፱/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. የ<u>ስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ መካከል ህዳር ፲ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም በአዲስ አበባና በሉግዘምበርግ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 89.795 ፀድቋል፡፡

**፫. <u>አስፈጻሚ አካላት</u>**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፴ ሚሊዮን ዩሮ (ሠላሳ ሚሊዮን ዩሮ) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፬ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "European Investment Bank Loan Agreement for financing Women Entrepreneurship Development Program Ratification Proclamation No. 1149/2019".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement Number 89.795 signed in Addis Ababa and Luxembourg on 19th Day of November 2018 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the European Investment Bank is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance</u>**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of equivalent to 30,000,000 Euro (Thirty Million Euro) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4 . <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On the 31th Day of July , 2019**

**SHALEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC**

**REPUBLIC OF ETHIOPIA**